# የገብረ መድህን ኑዛዜ እና ኢትዮጵያዊነት

ሕዝቅያስ ፍቅሬ

አዎ። አብዛኛዎቻችን የገብርዬን ኑዛዜ በወቅታዊ የኢትዮጵያውያኖች የመወያያ መድረክ ቃለምልልስ ላይ ያደመጥን መስሎ ይሰማኛል። እውነት ነው የምላችሁ ቃለምልልሱን ሳደምጥ ከገብርዬ አንደበት የሚወጣው የኢትዮጵያዊነት ስሜት እና ግልፅነት እጅግ ስሜቴን መቆጣጠር ከሚያደርሰኝ ደረጃ ላይ ነበር ያደረሰኝ።

እውነት ነው። ገብርዬ ወያኔ ነበር ለአስራ ስድስት አመት፤ በዚሁ አስራ ስድስት አመት በማወቅም ሆነ ባለማወቅ እንዴት ኢትዮጵያን ከወያኔ ጋር ሆኖ ያደማት እንደነበረ በቃለ መጠይቁ ላይ በሰፊው አትቷል። ነገር ግን ከቃለ መጠይቁ እንደተረዳሁት አብዛኛዎቹ የትግራይ ተወላጆችም ሆኑ እሱ በወያኔ ፀረ ኢትዮጵያ ጎራ ላይ የተሳተፉት በወያኔ ወደር የለሽ ተንኮል መሆኑን ግልፅ በሆነ አባባል ነበር ያስረዳ የነበረው። እንደ ገብርዬ አባባልም ወያኔ የትግራይን ህዝብ በዚሁ በፀረ ኢትዮጵያ ጎራ ላይ ለማሰለፍ እንዲያመቸው ኢትዮጵያን አፍቃሪ የትግራይ ተወላጆችን በይበልጥ አዛውንቶቹን አንድም ሳያስቀር ጄኖሳይድ እንዳደረገባቸው እጅግ በቁጭት ነበር ሲያወጋን የነበረው። ወያኔ የትግራይን ህዝብ በህውዜን ገበያ ላይ እንዴት እንዳስጨፈጨፈም በግልፅ አስረድቷል። ወያኔ የትግራይ ህዝብ ጠላት እንጂ ወዳጅ እንዳልሆነም አሳማኝ ሊሆኑ ከሚችሉ ማስረጃዎች ጋ አንድ ባንድ አስቀምጦልናል።

በመሰረቱ አቶ ገብረ መድህን በ 1982 ኢ.ም አካባቢ የኢትዮጵያን ህዝብ ላደረገው ጥፋት ይቅርታ ከልብ ጠይቆ እስካሁንም ድረስ ቃሉን ጠብቆ ያለ ኢትዮጵያዊ ነው። አቶ ገብረ መድህን እስካሁንም ድረስ ጥቂት የትግራይ ተወላጆች በፍራቻ ተሸብበው ነው እንጂ ወያኔን እጅግ እንደሚቃወሙ በግልፅ አስቀምጦልናል። ለዛም አባባሉ እኔ በግሌ ከልቤ አምኜዋለሁኝ። ምክንያቱም ከአባባሉ እንደተረዳሁት ወያኔ የአብዛኛውን የትግራይ ተወላጆችን ወገኖች ቤተሰብ ደርግ ሳይሆን እሱ እንደበላ እየተረዱ ያሉ ትግራዮች እንዳሉ በመረዳቴ ነው። ከዛውስጥም አንዱ ገብርዬ ነው። ገብርዬ ነፍሰ ጡሯን ባለቤቱን ወያኔዎች እንዴት እንደገደሏት በቃለ መጠይቁም ላይ አስረድቷል። ይህን ስሰማ ልቤ አዘነ፤ ተከዘ፤ አይ ወያኔ በቃ እርጉዝ፤ ህፃን፤ አዛውንት አይልም በቃ የሰው ህይወት ሲቀጥፍ አዘንኩ፤ ነገር ግን ገብርዬ የሷ መሞት አይቆጨኝም አለ፤ እኔ የሚቆጨኝ ምንም የማያውቁት ህፃናቶች ሲቀጠፉ ነው አለ። አዎ ወያኔ የትግራይን ህዝብን ልብ ለማግኘት ሲል ብዙ የትግራይ ህፃናቶችን ገና በለጋነታቸው ቀጥፏል። ለዛውም ምስክር እንዲሆነን የህውዜኑን የወያኔ ድራማ በግልፅ አስቀምጦልናልም ከጅምሩ አስረድቶናልም። ገብርዬ እንዳባባሉ ደርጎች አርቀው ማሰብ አለመቻላቸው ነው እንጂ ማክሸፍ እንደሚችሉ ነው። ነገር ግን ምን ያደርጋል ጨለማው ደርግ አርቆ ማሰብ ባለመቻሉ ነገሩ ሊሳካ እና ወያኔም የትግራይን ህዝብ ልብ ሊሰልብ እንደቻለ በግልፅ አስረድቶናል።

እቺ የህውዜን ትርኢት ለወያኔ እዬ ነው የማይባል እድል እንደከፈተችለትም ገብርዬ አስረድቷል፤ ወያኔዎችም ብልጥ ስለ ነበሩ ትርኢቱን በተንቀሳቃሽ ካሜራ በደንብ አድርገው እንዴት እንደቀዱት ገብርዬ በደንብ አድርጎ ነው ያስረዳው። ወያኔም ከዛ ጊዜ ጀምሮ አለም አቀፍ ሚዲያዎችን ሊስብ ቻለ፤ ደርግንም በአለም አቀፍ ሚዲያ ደህና አድርጎ አስወቀጠ። ወያኔዎችም በሰርጎ ገብ ወያኔዎች በመጠቀም የደርግን እድሜ አሳጠሩት። ለምሳሌ ያህል የፍስሀ ደስታን ተልእኮ ምን እንደነበረም ቁልጭ ባለ አማርኛ ነበር ሲያስረዳ የነበረው። አይ ገብርዬ እውነትም ገብርዬ ካነጋገሩም እንደተረዳሁት እጅግ የዋህም ግልፅም እንደሆነ ነው ለነገሩ እያ የገብርዬ አይነቱ ባህሪ የድሮ የትግራይ ልጆች ባህሪ ነበር፤ የዛሬን አያድርገውና ስለ ትግራይ ህዝብ እነ አሉላ አባ ነጋ ምስክሮች ናቸው። የሆነው ሆኖ ገብርዬ እያ በታሪክ የምናውቀውን ድንበሬ ቀይ ባህር ነው የሚለውን የትግራይን ህዝብ በምናቤ እንዳስብ ነበር ያደረገኝ። ለዚህም ገብርዬን እጅግ አመሰግነዋለሁኝ።

**የትግራይ ህዝብ ከገብርዬ ቃለምልልስ ምን ይማራል?**

በመሰረቱ እዬን የገብርዬ ቃለምልልስ እያንዳንዱ የትግራይ ተወላጅ ቢሰማው እጅግ ገንቢ ነው ብዬ ነው የማስበው። ብዙ ከአእምሮዋቸው የተሰወረውን ነገር ሊያሳያቸው ይችላል ብዬም አምናለሁ። የተቃዋሚዎችም ወገን ቃለምልልሱን በተቻላቸው መጠን ህዝብ እንዲሰማው ማድረግ አለባቸው። ወያኔም ይጠቀምባቸው የነበሩት ፕሮፓጋንዳ እነኚህንና የመሳሰሉትን ነው። ወያኔ በዛን ወቀት እዬን ያህል መስራት ከቻለ አሁን ያለው የተቃዋሚ ወገን ከዛ በላይ መስራት ይጠበቅበታል እላለሁኝ። እውነት ለመናገር እዬ የገብርዬ ቃለ ምልልስ የብዙ የዋህ ትግራይ ወገኖቻችንን ልብ ይመልሰዋል የሚል ግምት አለኝ። ወያኔም የትግራይ ህዝብ ጠላት እንጂ ወገን እንዳልሆነም ከቃለ ምልልሱና ከአንዳንድ ጭብጦች ይረዳል የሚል እምነት አለኝ።

መቼም እዬን ሰምቶ ወደ ስነ አህምሮው ያልተመለሰ የትግራይ ሰው ካለ፤ እንደ ገብርዬ አባባል አውቆ የተኛን ቢቀሰቅሱት አይሰማም አይነት ነውና እንደዛ አይነቱን ሆድ አደር ባንዳ በማለት አልፈዋለሁኝ። ገብርዬ ስለ ሆድ አደሮችም በሰፊው ተንትኗል። እንደ አገላለጹም አብዛኛዎቹ የትግራይ ተወላጆች የስርአቱ ተጠቃሚ ስለሆኑ ወያኔን እንደሚደግፉ እና የሌላው ብሄር ኢትዮጵያዊያን ከስራቸው እየተባረሩ በምትኩ የትግራይ ተወላጆች እንደሚሰገሰጉ ምስክርነት ሰጥቷል። ገብርዬን የመሳሰሉ ጥቂት የትግራይ ተወላጆችም ጩኸታቸው እዬ ነው። ምክንያቱም እንደዚህ አይነቱ አካሄድ ኢትዮጵያን እንደሚያፈራርሳት እና ትግራይንም እንደዚህ አይነቱ አካሄድ ከፍተኛ ዋጋ እንደሚያስከፍላት በመረዳታቸው ነው። አሁንም ቢሆን ቀኑ አልመሸምና የትግራይ ተወላጆች ነገሩን ከውል በማስገባት እና ለልጆቻቸውም ጠላትን አብዝተው ከመሄድ የገብርዬን አርአያነት በመከተል ዲሞክራሲት ኢትዮጵያን ለመገንባት ከፀረ ወያኔ ጎራ ጋ እንዲሰለፉ አጥበቄ እመክራለሁኝ።

**ወያኔ ይጠቀምባቸው የነበሩት ፕሮፖጋንዳዎች!!!**

አቶ ገብርዬ በጣም እንዳስረዳው ወያኔዎች የትግራይን ህዝብ ይቀሰቅሱበት የነበረው ቅስቀሳ **አማራው የትግራይ ህዝብ ጠላት ነው** በሚል ነው። ይገርማል። በወቅቱ የነበሩ የትግራይ ተወላጆች አማራው የትግራይ ህዝብ ወዳጅ እንጂ ጠላት እንዳልሆነ አጥብቀው መቃወም ሲጀምሩ ጄኖሳየድ እንዳደረገባቸው ኑዛዜውን አሰምቶናል። ወያኔም ታሪክ አዋቂዎችን የትግራይ አባቶች አንድ ባንድ ካስወገደ በሁዋላ፤ በወቅቱ ምንም የማያውቁትን የትግራይ ገበሬዎች **አማራ ጠላትህ ነው** በማለት ጭንቅላቱን በጥላቻ በመሙላት በአማራው ላይ ዘመቻቸውን ከዛን ግዜ ጀምረው እንደጀመሩት በግልፅ አስቀምጦልናል። አማራውንም ብናጠፋው ምንም እንደማይጎዳን ብንተወው ግን ለእኛ አደገኛ ነው በማለት አማራውን በተገኘው መንገድ እንዲያጠፉት ከፍተኛ ቅስቀሳ ወያኔ ያደርግ እንደነበረ ገብርዬ በየዋህ አንደበቱ አስረድቶናል፤ ገብርዬም ከህልሙ ሲባንን እዬንን አካሄድ በመቃወም ይመስለኛል ወያኔን መቃወም የጀመረው።

ቢሆንም ቅሉ፤ ገብርዬ እዬንን አይነቱን አባባል ባይለውም ወያኔ ስልጣን ከያዘ ጀምሮ በአማራው ላይ ያካሄደው ጄኖሳይድ ለዛ ምስክር ነው። አማራው ወያኔ ስልጣን ከያዘ ጀምሮ የወያኔ ሰለባ ሆኗል። በትግራይ ወገኖቻችንም ላይ እንደዚህ አይነቱ አመለካከት በከፊልም ቢሆን እንዲሰፍን አድርጓል። ኢትዮጵያንም ለመከፋፈያ በዋነኝነት ተጠቅሞበታል። እያንን እሬሳውን እንኩዋን በኢትዮጵያ ባንዲራ አሸሞንሙኖ የሚቀብር ህዝብ በኢትዮጵያዊነቱ እንዲያፍር እና እሱም በኢትዮጵያዊነቱ ከማንኛውም ህዝብ ጋ እንዳይተባበር አድርጎታል። ለዛም ምስክርነቱነቱን በ 97 ምርጫ ላይ በነበረው ጭፍጨፋ አረጋግጧል። በጭፍጨፋውም ወቅት ወያኔ አብረውት እንዲቆሙ አድርጎዋቸዋል። መቼም ታሪክ እንደሚያስተምረንም ሆነ በእድሜያችን እንዳየነው የመሀሉ አገር ህዝብ የትግራይ ህዝብ ከተነካ ለህይወቱ እንኳን ሳይሳሳ በፈንጂ ላይ እየተረማመደ

ነበር አጋርነቱን የሚገልፀው። የትግራዩ ግን ጀሮ ዳባ ብሏል፤ አሁንም ቢሆን ጊዜው አልጨለመምና እንደነገብርዬ እና እንደመሳሰሉት ውድ የትግራይ ልጆች ከወገናቸው የኢትዮጵያ ህዝብ ጋር በመቆም ታሪካዊ ጠላታቸውን ከህዝባቸው ጫንቃ ላይ እንዲያስወግዱ ወገናዊ ምክሬን እለግሳቸዋለሁኝ።

የአቶ ገብርዬን ኑዛዜ ባለፈው ግዜ ነካ ነካ አድርጌላችሁ ነበር። መቼም የገብርዬ ወግ ተፅፎ የሚያልቅም አይደለም። እንግዲህ በመጠኑም ቢሆን ካለፈው የተረፈውን የገብርዬን ወግ ጀባ ልበላችሁ።

ገብርዬ ከአሁን በሁዋላ በዘር ለተደራጀ ፓርቲ ድጋፌን አልሰጥም ነበር ያለው። እኔ በግሌ ስሜቴን የሳበኝ ነገር ቢኖር እዬ አይነቱ አባባል ነው። እጅግም ደስ አለኝ። በይበልጥ ከወያኔ ጎራ ከወጣ ሰው እንደዚህ አይነቱ ንግግር መውጣቱ በራሱ የሆነ ተአምራዊ ሀይል መስሎ ነው የተሰማኝ። በጣም ያልጠበኩት ንግግር ነበር። ስለ አረና ትግራይም ተጠይቆ ሲመልስ አረና ትግራይን ከወያኔ በምንም አይነት መልኩ ለይቶ እንደማያየው ነበር የገለፀው። አረናዎችም የጎጥ ፓርቲዎች ስለሆኑ መቼም ድጋፉን እንደማይሰጣቸው ነበር ሲያወጋን የነበረው። አዎ ገብርዬን ከንግግሩ እንዳነበብኩት ስሜተ ኢትዮጵያዊነቱ ከጎጡ አይሎ እንደወጣ ነው የተረዳሁት፤ እረ ብዙ ብሎናል፤ ስለነ ስዬ አብርሀምም፤ ስለነ አብርሀ ያየህም ብዙ አውግቶናል በቁጭት፤ አብርሀ ያየህንማ የምላስ አርበኝነቱንና ሞላጫነቱን በየዋህ አንደበቱ አውግቶናል። አቶ ገብርዬ እንዳለው በወያኔ ውስጥ የነበሩ አመራሮች በአጠቃላይ እጃቸው በደም የተጨማለቀ እንደሆነ በሰፊው አትቷል። እንዳባባሉም ለዛ ሁሉ ወንጀል ህዝብ ፊት ተንበርክከው ይቅርታ መጠየቅ አለባቸው በማለት አስረግጦ ነግሮናል።

አቶ ገብርዬ ስለ ስዬ ተጠይቆ ሲመልስ፤ ስዬ የበላይ አለቃውና ከፍተኛ ባለስልጣን እንደነበረ ነው ያስረዳን፤ ከፈላጭ ቆራጮቹ አንዱ እንደነበረም ገልጿል። በመሰረቱ አቶ ስዬ አብርሀ በግልፅ ኢትዮጵያን ይቅርታ የጠየቁበትን መድረክ አልሰማሁም፤ የሳቸው ስሜት የስርዓተ ለውጥ ሳይሆን የጥቂት ሰዎች ለውጥን መሻት መስሎ ነው የሚሰማኝ። ለነገሩ አቶ ስዬ አንድ ቀን እንደ ገብርዬ ወደ ስነ አእምሮዋቸው ተመልሰው የኢትዮጵያን ህዝብ በድዬሀለሁኝ ማረኝ ብለው ይጠይቃሉ የሚል እምነት ስላለኝ ስለሳቸው ብዙ ለማለት አልደፍርም። አቶ ገብርዬ ስለነ አቶ ታምራት ላይኔ እና መሰሎቹም አውግቶናል፤ ያሳዝናል፤ ታምራት ላይኔ ከ **5000 በላይ የኢህአፓ ሰዎችንም እንዴት እንዳስፈጀ ጀባ ብሎናል።** እሱ እንዳለው የወያኔ የዘር ፍጅት የጀመረው ከኢህአፓ ባይሆንም የኢህአፓን ልዩ የሚያደርገው እንዲህ ነው በማለት ነበር ወጉን የጀመረው፤

አህአፓ የአማራ ተወላጆች ስብስብ ይበዛዋል ከሚል ጭፍን ዘረኝነት በመነሳት ከኢህአፓ ባፈነገጡ በነ ታምራት ላይኔ፤ አዲሱ ለገሰ፤ ህላዌ ዮሴፍ እና በመሳሰሉት ቀንደኛ የኢትዮጵያ ጠላቶች ጋር በመተባበር እንዴት ኢህአፓን እንደጨፈጨፉ በየዋህ አንደበቱ አስረድቶናል። እኛ ደግሞ እንደሰማነውና እንዳነበብነው ከሆነ የኢህአፓ ማእከላዊ ኮሚቴ አባላት የነበሩት ብርሀነ መስቀል ረዳ፤ ተስፋዬ ደበሳይና ሌሎችን ስማቸውን በውል የማላስታውሳቸው ሰዎች የትግራይ ተወላጆች እንደነበሩ ነው። ታዲያ ምነው እነመለስና አረጋዊ በርሄ የመሳሰሉት ወያኔዎች አማራውን በማያውቀው ነገር የዛ ሁሉ እዳ ተሸካሚ አድርገው ጨፈጨፉት፤ አጃኢብ ነው። ለነገሩ በዘር ማሰብ ከተጀመረ ከዛ እንደማይዘል የአለም ታሪክም ቢሆን ቁልጭ አድርጎ ነው የሚያሳየን፤ ሂትለርም ለዛ ምስክር ነው። የስድስት ሚሊዮን ይሁዳዊም ህይወት የተቀጠፈው በዘር ስሌት በመታሰቡ ነው። እጅግ ሊወገዝ የሚገባው አደገኛ ነገር ነው። የገብርዬም ሀሳብ የዘረኝነት ስሌቱ ጥፋት እንጂ ልማት እንዳልሆነ በግልፅ አማርኛ አስረድቶናል።

**ዘረኝነትን እንዴት እንዋጋለን?!**

ከላይ እንደገለፅኩት አቶ ገብረ መድህን ለዛ መልስ ሊሆን የሚችል ነገር በግልጽ አስቀምጧል። "እኔ የዘር ፓርቲ ከአሁን በሁዋላ አልደግፍም በማለት"፤ ኢትዮጵያዊ የሆነውን ድርጅት ግን አንዱንም አልቃወምም ነበር ያለው ፤ እዬ አባባል በእውነቱ ሁሉንም ታዳሚ ነበር ያስደመመው። አቶ ገብረ መድህን የዋህ ብቻ ሳይሆን አዋቂም ነው፤ የአለምን የፖለቲካ ሁኔታም በደንብ አድርጎ የተገነዘበ ሰው ነው ከንግግሩ እንደሰማሁት ከሆነ፤

አቶ ገብረመድህን በመድረክ የተሰባሰቡትም ከዛ ስሌት እንደማይዘሉ ጨረፍ ጨረፍ አድርጎልናል። ለነገሩ እውነት ነው ስሌቱ። ከድብብቆሽ ህይወት እንውጣ ብለን ካሰብን በመድረክ ወስጥ የተሰባሰቡት ክምችቶች ከ UDJ በስተቀር ሁሉም የዘር ቀመሮች ናቸው። አይ ኢትዮጵያ፤ ምነው ምንይልክ ጉድሽን አልሰሙሽም ነበር ያልኩት፤ ለነገሩ ለእኔ እነኚህ ጎጠኞች የትም እንደማይደርሱ ሳስበው ጡንቻዬ ይፍታታል፤ የራሳቸው ነገር እራሳቸውን ነው እንጂ ማንንም እንደማይበላ ሳስበው ብዙም አልጨነቅበትም። ይልቁንስ በቅዠት ከሚዋዥቁበት አለም ወጥተው የአንድነት ሀይሉን ይቀላቀሉ ዘንድ መልካም ምኞቴ ነው። ሁሉም የተቃዋሚ ፓርቲም ቢሆን ከእንደነዚህ አይነቶቹ ጋ ወርቃማ ጊዜውን ከሚያጠፋ ከአንድነት ሀይሎች ጋ በመተባበር የኢትዮጵያን ህዝብ የመከራ ዘመን ያሳጥሩት ዘንድ ምክሬን ጀባ እላቸዋለሁኝ። የዛን ግዜም የአንድነት ሀይሉ ሲጠናከር እና የሀይል ሚዛኑ ሲያመዝን በማወቅም ሆነ ባለማወቅ በዘር የተደራጁ ፓርቲዎች ማጣፊያው ሲያጥራቸው ወደ አንድነት ሀይሉ ይመጣሉ የሚል ግምት አለኝ። የዛን ግዜ ነው እንግዲህ ዘረኝነትን ከኢትዮጵያ ምድር ጠራርገን ልናወጣ የምንችለው።

**ገብረ መድህን በስልጣን ዘመኑ**

እንዳልኩዋችሁ አቶ ገብርዬ ብዙ ብዙ ብሏል። ሁሉንም ለመፃፍ የግዜ ችግር አለ። ይሁን እንጂ እኔ በተቻለኝ መጠን ጠቅለል ባለመልኩ ነው ሀሳቤን እያሰፈርኩ ያለሁት። ሌላው ደግሞ እንዲህ ነበር ያለው። አዎ የወያኔ ገንዘብ ያዥ እያለሁ አዜብ መስፍንን በግል ህይወቷ ሳይቀር አውቃታለሁ ነበር ያለው፤ የመለስ ሚስት ስለሆነች ብቻ ገንዘብ በጎን እየመጣች አምጣ እያለች ታስቸግረኝ ነበር ያለው። ገብርዬም እንዳወጋን ከሆነ እምቢ ሲላት ለስብሀት ነጋ ክስ አቅርባ እንደነበረ እና ስብሀትም ምክንያቱን እንደጠየቀው ነው። የሆነው ሆነና እያ እኔን አይመለከተኝም፤ ነገር ግን ቀልቤን የሳበኝ ነገር ቢኖር አዜብ መስፍን አባቷ ሱዳናዊ መሆኑ ነው እያንንም ነገር በእርግጠኝነት ነበር ሲናገር የነበረው። በእርግጥ እናቷ የወልቃይት ጠገዴ ሰው እንደሆነችም ምስክርነቱን ሳይደብቅ ሰጥቷል። ብቻ የወያኔ ጉድ ብዙ ነው። ተፅፎም የሚያልቅ ጉዳይ አይደለም። ይሁን እንጂ በዚህ ጉዳይ ላይ ወደፊት መረጃዎችን ጸሀፊዎቻችን አሰባስበው ጀባ ይሉናል የሚል እምነት አለኝ።

ይህ በእንዲህ እያለ፤ ወደማጠቃለያው ሳመራ አቶ ገብረመድህን እጅግ ሀቀኛ ኢትዮጵያዊ እንደሆነና ለዚህ ለሰጠው ምስክርነትም እጅግ በጣም በግሌ ሳላመሰግነው አላልፍም። እናንተንም ወገኖቼን በቸር እስክንገናኝ ድረስ ሰላም ሁኑ በማለት ለዛሬ በዚህ እሰናበታችሁዋለሁኝ።

ሕዝቅያስ ፍቅሬ (agere_ethiopiaa.com)
(Source: www.abugidainfo.com)